NEWA

UN WOMEN

# የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ




Credit:UN Women Cartoon competition 2nd place winner, Binyam Wondemagegnehu, 2018

## በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መረዳት፣ መከላከልና ምላሽ መስጠት

03 የካቲት 2017 ዓ.ም

# በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መረዳት፣ መከላከልና ምላሽ መስጠት

## የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ



Credit: UN Women Cartoon Competition 3rd place winner, Yonatan Seyoum, 2018

03 የካቲት 2017 ዓ.ም

# ማውጫ

1.ዓላማ ---------------------------------------- 2
2. በምርጫ ወቅትናማውጫ በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መረዳት ------------------------------ 3
2.1 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶች ---------- 5
2.2 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ አካላት -------- 6
2.3 በምርጫ ወቅት ጥቃት ሊደርስባቸው የሚችሉ ሴቶች ----------- 7
2.4 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ጥቃት የትና መቼ ይፈጸማል ----------- 7
2.5 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጥቃት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች -------------------------------------- 7
2.5.1 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት የሚያስከትላቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው? ---------------------------------- 8
3. በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈጸም ጥቃት ያሉ እውነታዎች -------- 9
4. በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ለምን መሰራት ያስፈልጋል? --------------------------- 11
5. በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መቼና እንዴት መፍታት ይቻላል? -------------------------- 11
5.1 በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መቼ መፍታት ይቻላል? ----------------------------- 12
5.2 በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል እንዴት መሰራት ይቻላል? ------------------ 13
6. በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ምላሽ መስጠት የሚችሉ አካላት እነማን ናቸው? ------------------ 16

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1.
በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች - - - - - 4
ሰንጠረዥ 2.
በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶች - - - - - - - - - - - - - - 5
ሰንጠረዥ 3.
በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ አካላት - - - - - - - - 6
ሰንጠረዥ 4.
በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጥቃት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች - - - 8
ሰንጠረዥ 5.
በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት የሚያስከትላቸው ችግሮችና የሚያደርሰው ተጽእኖ - - - - - - - - - - - - - - - - 8
ሰንጠረዥ 6.
በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ ህጎችና ያሉ ክፍተቶች - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 14

## 1. ዓለማ

ዓለም-አቀፍ የምርጫ ስርዓት ፋውንዴሽን (IFES) ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን (VAWIE) በተመለከተ ያካሄደው ጥናት ኢትዮጵያን ጨምሮ በዓለም-አቀፍ ደረጃ የእውቀት፣ የምርምርና የመረጃ አጥረትን አጉልቶ ያሳያል። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና በተባበሩት መንግስታት የሴቶች ድርጅት (ዩኤን ውሜን) አማካኝነት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶችን፣ መንስኤዎችንና የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ለመለየት የሚያስችል ጥናት በተመረጡ ክፍለ ከተማዎች ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎች ማለትም ከአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ-ከተማ፣ ከአማራ ክልል ባህር ዳር ዙሪያ፣ ከኦሮሚያ ክልል አዳማ ዙሪያ እና ከደቡብ ክልል በወልቂጤ ተካሂዷል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በሁሉም የምርጫ ዑደቶች ላዩ የሚያጋጥም ሲሆን የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ-ምርጫ ወቅት ፣ በምርጫ ዕለት እና በድህረ- ምርጫ ወቅት የደረሱ የተለያየ መልክ ያላቸው ጥቃቶችን ሪፖርት አድርገዋል። በዋነኝነት የጥቃቱ ፈጻሚዎች ወንዶች ሲሆኑ ይህም የቤተሰብ አባላትን፣ መራጮችንና የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን የሚያካትት ሲሆን ጥቃቱ በሁለቱም ማለትም በቤት ውስጥና ህዝብ በሚሰብሰብባቸው ቦታዎች ላዩ ይፈጸማል። ለጥቃቱ መፈጸም አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ በባለድርሻ አካላትና በምርጫ አስፈጻሚ አካላት መካከል በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በመከላከልና የምላሽ አሰጣጥ ዘዴን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆን፣ የህግ ማዕቀፎች ክፍተት እና በቁጥር አንስተኛ የሆኑ ቡድኖችን የሚጎዱ የብሔር የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ተጠቃሽ ናቸው።

በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችንና ተያያዥ ጉዳዮችን ለመፍታት የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) እና የተባበሩት መንግስታት የሴቶች ድርጅት (UN WOMEN) በኢትዮጵያ ይህንን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በማዘጋጀት በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ ውስጥ በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ የጥቃት ዓይነቶችን፣ መንስኤዎችና የሚያስከትሏቸውን ችግሮች በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር፤ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት እንደሚጎዱ ግንዛቤን ማሳደግ ብሎም ችግሩን እንዴት መከላከልና መፍትሄ መስጠት እንደሚቻል መመሪያ ለመስጠት እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ ውስጥ በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚተገበሩ መርሃ-ግብሮችን አፈዓፀም እንዲደግፉ ለማድረግ ያለመ ነው።

ይህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ብሎም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በፖለቲካ ውስጥ እንዲሁም በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከል እንዲችሉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ብሎም በኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመፍታት ዋነኛ ተብለው በሚታሰቡ የፍትህ ተቋማት መካከል ያለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት ያለመ ነው።

## 2.በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መረዳት

በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የተለያዩ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች አእንዳሉ የሚታወቅ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች (VAWiP) እና በምርጫ ጊዜ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት (VAWiE) ይገኙበታል፡፡ በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ከሌሎች የጥቃት ዓይነቶች እንዴት እንደሚለዩ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያሉት ትርጓሜዎች ከፖለቲካና ከምርጫ ጋር የተያያዙ የተለያዩ የጥቃት ምድቦችን በግልፅ ያሳያሉ፡፡

በፖለቲካ ተሳትፎ ወቅት ሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ማለት ማንኛውም ፆታን መሰረት ያደረገ፤ ሴቶች የፖለቲካ መብቶቻቸውን ማለትም በምስጢር የመምረጥ፣ የመመረጥ፣ ህዝብን የማስተዳደር፣ የምርጫ ቅስቀሳ የማድረግ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ሃሳብን በነጻነት የመያዝ ወይንም የመግለጽ መብቶቻቸውን በአደባባይም ሆነ በግል ህይወታቸው እንዳይጠቀሙ የሚያግዳቸው አካላዊ፤ ወሲባዊ ወይም ስነልቦናዊ ጉዳት የሚያደርስ ፆታን የማከለ ጥቃት ወይም ጥቃት ለማድረስ ማስፈራራት ነው፡፡

የኤን ውሜን እና የኤንዲፒ አ.ኤ.አ 2018, በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከል የፕሮግራም መመሪያ

ሰንጠረዥ 1. በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ ተሳትፎ/እንቅስቃሴ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ትርጉም

| የጥቃት ዓይነት | ትርጉም | ዋና ባህሪያት | ጉዳት የሚደርስበት አካል ማን ነው? |
| --- | --- | --- | --- |
| በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት (VAWiE) | ሴቶች በምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፋቸው ምክንያት ጾታን  መሰረት አድርጎ የሚደርስ በሴቶች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ነው። | - የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለመገደብ ያለመ ሲሆን - አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ወሲባዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ሊሆን ይችላል። - በሁሉም የምርጫ ዑደቶች (ቅድመ-ምርጫ፣ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜና ድህረ-ምርጫ) ወቅት ይከሰታል። | - ሴት መራጮች፣ እጩዎች፣ ታዛቢዎች፣ የምርጫ ሰራተኞች፣ የጸጥታ አካላት፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲ (አባላት፣ ደጋፊዎች፣ ተወካዮችና አመራሮች) |
| በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት (VAWiP) | ሴቶች ከምርጫ ባለፈ በፖለቲካ ህይወት ውስጥ የሚደርስባቸው ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው። | -በምርጫ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ይከሰታል። ትንኮሳ፣ ዛቻና መድልዎን ያካትታል። | - ሴት ፖለቲከኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ አክቲቪስቶች፣ የመንግስት ባለስልጣናት |
| ምርጫን የተመለከተ ጥቃት | በሁሉም የምርጫ ሂደቶች ውስጥ የሚሳተፉ ወንዶችንና ሴቶችን የሚያጠቃ ፖለቲካዊ ጥቃት ነው። | - ይህ በምርጫ ውጤት ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ያለመ ሲሆን። - የድምጽ ማጭበርበርን፣ ማስፈራራትን፣ ብጥብጥ ማንሳትን ሊያካትት ይችላል። በሁለቱም ጾታዎች ላይ ያነጣጠረ ነው፣ ነገር ግን ባልተመጣጠነ ሁኔታ በሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል። | - ሁለቱም ወንዶችና ሴቶች (ነገር ግን ሴቶች ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ ከፍተኛ ተጽእኖ ይደርስባቸዋል) ። |

በምርጫ ወቅት ሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ሴቶች የፖለቲካ መብቶቻቸዉን በተለይም በምርጫ ዑደት ውስጠ እንዳዩጠቀሙ እንቅፋት የሚሆነ የሴቶች ጥቃት አይነት ነው። ይህ አይነቱ ጥቃት ሴቶች ተመራጭ፣ መራጭ፣ የማህበረሰብ አንቂ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊ፣ የምርጫ ታዛቢ፣ የምርጫ አስፈጻሚ፣ ወይም የመንግስት ባለስልጣን እንዳይሆኑ ለማድረግ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን የጨምራል።

የኤን ውሜን እና የኤንዳፒ እ.ኤ.አ 2018, በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከል የፕሮግራም

## 2.1 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶች

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ በርካታ የጥቃት ዓይነቶች ሲኖሩ ከነዚህም ውስጥ፡- ስነ-ልቦናዊ ጥቃትና ማስፈራራት፣ ወሲባዊ፣ አካላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዠ በዝርዝር ተገልፀዋል።

ሰንጠረዥ 2. በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶች

| የጥቃት ዓይነት | መግለጫ | ምሳሌ | የት ይከሰታል |
|---|---|---|---|
| ስነ-ልቦናዊ ጥቃት | ይሄ በተደጋጋሚና በተለያየ ሁኔታ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም የጥቃት አይነት ነው። ዓላማውም ሴትን ለማስፈራራት፣ ለማንገላታት፣ ለመበደል፣ ለማሸማቀቅ፣ ዝቅ ለማድረግ ወይም ሴትን ለማሳፈር ታስቦ የሚደረግ ጥቃት ነው። | ስም ማጥፋት፣ ሴት ፖለቲከኞች ተቀባይነት እንዳያጡ ባህሪያቸውን አጠልሽቶ የሚያሳዩ ዘመቻ፣ ስድብ፣ ዛቻ፣ የጥላቻ ንግግር፣ ትንኮሳ (በመገናኛ ብዙኃን/በማህበራዊ ድረ-ገጾች ጭምር)፣ ማስፈራራት፣ ማንቋሸሽ፤ የውሸት ውንጀላ፣ በሰውነት አቋም ማሸማቀቅ እና ጫና ማሳደር። | በቤት ውስጥ፣ በማህበረሰብ ደረጃ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች በዩነ-መረብንም ይጨምራል። |
| አካላዊ ጥቃት | ኃይልን በመጠቀም ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትል የሚችል ጥቃት ነው። | መግፋት፣ መጎተት፣ መምታት | በቤት ውስጥና ህዝብ በሚሰበሰ ብባቸው ቦታዎች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወሲባዊ ጥቃት | ተቀባይነት/ስምምነት የሌላቸው ወሲባዊ ድርጊቶች፣ ወሲባዊ ጥያቄዎች ወይም ትንኮሳዎች ናቸው። | ወሲባዊ ጥቃት፣ አስገድዶ መድፈር፣ በደል፣ ትንኮሳ፣ የወሲብ ነክ የሆኑ የማይፈለጉ አስተያየቶችን መስጠት፤ | በቤት ውስጥና ህዝብ በሚሰበሰ ብባቸው ቦታዎች በዩነ- መረብንም ይጨምራል። |
| ኢኮኖሚያዊ ጥቃት | በገንዘብና በሀብት ላይ የሚደረግ ቁጥጥርና የንብረት ውድመት ነው። | የገንዘብ ሀብትን መከልከል ወይም ማዘግየት እና የንብረት ውድመት ማድረስ; ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል ገንዘብ መከልከል። | በቤት ውስጥና ህዝብ በሚሰበሰ ብባቸው ቦታዎች (የስራ ቦታንም ጨምሮ) |

## 2.2 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ አካላት

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት በግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የመንግስት አካላት አማካኝነት ሊፈጸም ይችላል። ጥቃት ፈጻሚዎች/አድራሾች ወንድ ወይም ሴት፣ የቤተሰብ አባል ወይም አባላት ያልሆኑ እንዲሁም ግለሰብ ወይም ቡድን ሊሆኑ ይችላሉ። የጥቃት ተዋናዮችና ፈጻሚዎች ሊሆኑ የሚችሉ ተብለው የሚጠቀሱ አካላት ከምሳሌዎች ጋር ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 3. በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ አካላት

| ምድብ | በጥቃት አድራሽነት ተዋናይ ሊሆኑ የሚችሉ አካላት | ምሳሌ |
|---|---|---|
| ቤተሰብ | የትዳር አጋር፣ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህት፣ አማቶች፣ የአጎትና አክስት ልጆች | ባል ሚስቱን ምርጫ እንዳትመርጥ መከልከል |
| ማህበረሰብ | የወንድ ጓደኛ፤ መራጮች፣ የሐይማኖት መሪዎች፣ ባህላዊ መሪዎች፤የማህበረሰብ አባላት፣ ሚዲያ፣ አሰሪዎችና የስራ ባልደረቦች፣ የማህበረሰብ አንቂዎችና የወጣት ቡድኖች፤ ጋዜጠኞች፤ የመገናኛ ብዙሃን ሰራተኞች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ የወንጀል ቡድኖች ወይም የታጠቁ ሃይሎች | አክቲቪስቶች ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ሴት እጩን ማዋከብ/ትንኮሳ መፈጸም |

| | | |
|---|---|---|
| ፖለቲካዊ | የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ መሪዎች፣ የምርጫ እጩዎች፣ ቅስቀሳ አድራጊዎች፣ ወኪሎች፤የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች | በስልጣን ላይ ያለ ፓርቲ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ የሆነችን ሴት እጩ ማስፈራራት |
| የመንግስት አካላት | የሕግ አስከባሪ አካላት (ፖሊስ፣ ታጣቂዎችና የጸጥታ አስከባሪ አካላት) የመንግስት አካላት፣ የምርጫ አስፈዓሚዎች፣ ቀሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፤ የደህንነት አካላት | የጸጥታ አስከባሪ አካላት ሴት መራጮችን ማስፈራራት |

## 2.3 በምርጫ ወቅት ጥቃት ሲደርስባቸው የሚችሉ ሴቶች

በምርጫ ወቅት ጥቃት ሲደርስባቸው የሚችሉ ሴቶች ዕድሜያቸው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑና በምርጫ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆኑ ይችላሉ። ከነዚህም መካከል፦

- ✓ሴት መራጮች፣
- ✓የምርጫ እጩዎችና አስፈጻሚዎች፣
- ✓የፓርቲ ተወካዮች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ ስራ አስፈዓሚዎች፣
- ✓ታዛቢዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ቅስቀሳ አድራጊዎች እና
- ✓በምርጫ የሚሳተፉ ሴቶች የቤተሰብ አባላት
- ✓የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊዎች፣ አነቃቂዎች ወይንም የምርጫ ቅስቀሳ የሚያካሂዱ ሴቶች
- ✓መንግስትን ወክለው የምርጫ ስራዎችን ለማሳለጥ የሚሰሩ ሴቶች
- ✓የምርጫ ሂደት የሚዘግቡ ሴት የመገናኛ ብዙሃን ሰራተኞች፤ በምርጫ ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች

## 2.4 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ጥቃት የትና መቼ ይፈጸማል

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በቤት ውስጥ ወይም ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ማለትም በምርጫ ጣቢያዎች፣ በሥራ ቦታዎች፣ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ለመሄድ ወይም ለመመለስ በሚያደርጉት ጉዞ ላይ ለምሳሌ በቅድመ ምርጫ ወቅት (በምዝገባ ጊዜና በምርጫ ቀን ማብቂያ/ምሽት አካባቢ) እንዲሁም በሁሉም ቦታና በማንኛውም ጊዜ የሚፈጸም ጥቃት ነው።ይህ ጥቃት በአካል (ፊት ለፊት) ከመድረሱ በተጨማሪ በመደበኛ እና በማህበራዊ የሚዲያ ዘዴዎች ማለትም እንደ ፌስቡክ፣ ኢንስታግራም፤ ትዊተርና፣ የሞባይል አጭር የጽሁፍ መልእክት ፣ የትዩብ፣ ብሎጎች እና በሕትመት/ጽሑፍ፣ በንግግር፣ በቪዲዮ ወይም በስዕል በመጠቀም ሲደርስ ይችላል።

## 2.5 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጥቃት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች

ባህላዊ፣ ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ጨምሮ በርካታ ነገሮች በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጥቃት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዠ የተለያዩ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ነገሮችን ይዘረዝራል።

ሰንጠረዥ 4. በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጥቃት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች

| ምክንያቶች | መግለጫ | ምሳሌ |
|---|---|---|
| ባህላዊና ማህበራዊ አመለካከቶች | ሴቶችን ከፖለቲካ ተሳታፊነት አግልሎ የወንዶች የበላይነት የሚያራምድ አስተሳሰብ/አመለካከት/እምነት እንዲሁም የፖለቲካ ባህል፤ ግጭት የበዛበት የፖለቲካ ባህል | ሴቶች ለመሪነት ብቁ እንዳልሆኑ አድርጎ ማየት፤ ብሎም ሴቶች በፖለቲካና በህዝብ አስተዳደር ያላቸውን ሚና ዝቅ አድርጎ መሳል፤ |
| የምርጫ አስተዳደር ላይ ያሉ ክፍተቶች | ሴቶችን ለአደጋ የሚያጋልጥ ወይም ጥበቃ ለማድረግ በቂ ዝግጁነት የሌለው ተቋማዊ አደረጃጀት | ሴት የጸጥታ ሰራተኞች እጥረት/እናሳ መሆን፣ በምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተሻለ መብራት/ብርሃን አለመኖር፣ አንድ ብቻ የወረፋ መስመር (ለወንዶችና ለሴቶች) መኖር፣ በጣም ቀደም ብለውና በጣም ዘግይተው ድምጽ መስጠት፣ የምርጫ ጣቢያው ረጅም ርቀት ያለው መሆንና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጥቃት ሪፖርት ማድረጊያ ዘዴ አለመኖር |
| በሕግ እና በፖለቲካ የሚስተዋሉ ውስንነቶች/ድክመቶች | ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ ሕግ አለመኖሩ ወይም ያሉት የሕግ ማዕቀፎች በበቂ ሁኔታ አለመተግበራቸው | በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ግልጽ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር |

## 2.5.1 በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት የሚያስከትላቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው?

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተለያዩ ጥቃቶች ይደርሳሉ፤ ለምሳሌ፦ ስነ-ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የጤና ጉዳዮችን የሚጎዳ ሲሆን ከዚህ በታች እንደተመለከተው በሴቶች፣ በቤተሰባቸውና በማህበረሰቡ ላይ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ ችግሮችን ያስከትላል።

ሰንጠረዥ 5. በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት የሚያስከትላቸው ችግሮችና የሚያደርሰው ተጽእና

| የሚያስከትላቸው ችግሮች | የሚያደርሰው ተጽእኖ/ችግር |
|---|---|
| አካላዊ ጉዳት | የአካል ጉዳት፣ ስብራት ወይም ሞት |

| | |
|---|---|
| ኢኮኖሚያዊ ውድመት | የገቢ ማጣትና የገንዘብ ችግር |
| ማህበራዊ ቀውስ | የትዳር መበተን ወይም የቤተሰብ መፍረስ |
| የፖለቲካ ተሳትፎ መቀነስ | ፖለቲከኛ መሆን የሚመኙና ለምርጫ የሚወዳደሩ ሴቶች አናሳ መሆን |
| የድምጽ አሰጣጥ ተደራሽ አለመሆን | ሴቶች ምርጫ እንዳይመርጡ መደረግ |
| የምርጫ ሂደቱ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ደካማ መሆን | ሴት የምርጫ ሰራተኞችና ታዛቢዎች አነስተኛ መሆን፤ ሴቶች በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ የቀነሰ መሆን (ለምሳሌ የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አለመፈለግ፤ ወጥቶ ድምፅ የመስጠት ፍላጎት መቀዛቀዝ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሪ ወይም ተጠሪ መሆን አለመፈለግ) በአጠቃላይ ከምርጫ ጋር የሚያያነኩ ጉዳዮች ላይ ፍላጎት መቀነስ። |

## 3.በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ የሚፈጠሩ ጥቃቶች ላይ ናሙና መረጃዎች

በዩ ኤን ውመን የተዘጋጀው በፖለቲካ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን መከላከል መመሪያ የተለያዩ ሃገራት ላይ የተሰሩ ጥናቶችን ዋቢ አድርጎ በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በሴቶች ላይ የተፈጸሙ የጥቃት ክስተቶችን አካቶ ይዟል። ከእነዚህ የጥቃት ክስተቶች በጥቂቱ ማሳያ ይሆኑ ዘንድ በከፊል ከታች ተዘርዝረዋል።

### በዓለም-አቀፍ ደረጃ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች

- **ኮሎምቢያ (እ.ኤ.አ 2016)፡-** 63% የሚሆኑት ሴት የምርጫ ተወዳዳሪዎች በአብዛኛው በባልደረቦቻቸውና በተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ በሚገኙ ወንዶች በተፈፀሙ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ሰለባ መሆናቸውን ተናግረዋል።
- **እ.ኤ.አ በ2018** በሊባኖስ በሴቶች ላይ የተፈጸመ የድህረ-ምርጫ ጥቃት፡- 87% የሚሆኑ ሴት እጩዎች የስነ-ልቦና ጥቃት (ዛቻ፣ ስድብና የበይነ- መረብ ወሲባዊ ትንኮሳንም ጨምሮ) እንዳጋጠሟቸው ሪፖርት አድርገዋል።

### በአፍሪካ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች

- **ታንዛኒያ (እ.ኤ.አ 2015)፡-**
    - ወደ 69% የሚሆኑ ሴት እጩዎች ጎጅ የሆነ/የሚያሸማቅቅ ስድብ አጋጥሟቸዋል ስድብ፣ ዘለፋ፣ ማሸማቀቅና በመድረክ ላይ አየሁ የሰዎች ጩኸት) ።
    - በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ባሎችና የቤተሰብ አባላት ሴቶች ማንን መምረጥ እንዳለባቸው የማዘዝ አዝማሚያ ታይቷል።

---

[1] የኤን ውሜን፣ እ.ኤ.አ 2021, በፖለቲካ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከል መመሪያ

[2] የኤን ውሜን፣ እ.ኤ.አ 2016, በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች፣ (እ.ኤ.አ በ2015 ከተካሄደው የታንዛኒያ አጠቃላይ ምርጫ የተገኘ መረጃ)

- ኬንያ፦ ሴት የምርጫ እጩዎች ለምርጫ ቅስቀሳ ሲወጡ ድብደባ፤ አስገድዶ መድፈር፤ ስድብ፣ ጠለፋና የግድያ ዛቻዎች እንደሚደርስባቸው ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች:- ከስድስተኛው የሃገራዊ ምርጫ በኋላ የተወሰኑ ክልሎችን መሰረት አድርጎ የተሰራ ጥናት እንደሚያሳየው [ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስእ.ኤ.አ 2023፣ በኢትዮጵያ በአራት ክልሎች ማለትም አዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ የተሰራ ጥናት] ኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ ዑደት ውስጥ የሚፈፀመም ፆታን መሰረት ያደረገ ጥናት አለ። ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ጥያቄዎች መልስ የሰጡ ሴቶች እንደገለፁት ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተለዩ በምርጫ ቀን፣ ከምርጫ ቀን በፊት እንዲሁም በኋላ ይደርሳል።

- በጥቃቱ ተሳታፊ የነበሩ ሴቶቸ እንደገለፁት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ከተፈጸሙ የጥቃቶች ዓይነቶች ውስጥ በአብዛኛው ስነ-ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ወሲባዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ናቸው።
- ስነ-ልቦናዊ ጥቃት በጣም የተለመደው የጥቃት አይነት ሲሆነ አካላዊ፤ ወሲባዊ እንዲሁም የኢኮኖሚ ጥቃቶች ይደርሳሉ። ጥቃት አለ የተሰራ ጥናት እንደሚያሳየው በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶች በማስፈራራትና ሴቶች ምርጫቸው ያልሆነን ፓርቲ እንዲመርጡ በማስገደድ ነበር።
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ አካላዊ ጥቃት ዓይነቶች በድብደባና አንዳንድ የማሰቃየት ሁኔታዎችን በመጠቀም ሲሆን ወሲባዊ ጥቃት የተፈፀመው ደግሞ በትንኮሳ ሲሆን በአብዛኛው በቃል የሚፈፀሙ ናቸው።
- ከኢኮኖሚያዊ ጥቃቶች ውስጥ የቤት ንብረቶችንና ባለ ሶስት ጎማ ተሽከርካሪዎችን “(ባጃጆችን)” በማቃጠል የተፈጸመ ሲሆን እነዚህ ድርጊቶች የተፈፀሙት እጩዎችን ተስፋ ለማስቀረጥና ከዕጩነት እንዲለቁ ለማስገደድ ብሎም የመራጮችን ተሳትፎ ለመቀነስ ነው።

ለጥናቱ ቀልፍ መረጃ ከሰጡ ሴቶች እና ወንዶች እንዲሁም  የአትኩሮት ቡድን ውይይት (FGD) ተሳታፊዎች እና የንጥል ጥናት (Case Study) ተሳታፊዎች (ሁሉም ሴቶች) የተገኘው የዓይነታዊ ምርምር መረጃ እንደሚያሳየው በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በሚከተለው መልኩ ተፈጽመዋል፦

- እንደ መራጭ፣ እጩ፣ ታዛቢ፣ የምርጫ ቦርድ፣ የምርጫ አስፈጻሚ፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ወዘተ እንዳዩሳተፉ ማስገደድ፣
- የሴት እጩዎችን ፖስተሮች መቀደድ/ማንሳት፣
- የገዢውን ወይም የአውራ ፓርቲ እጩዎችን እንዲመርጡ ማስገደድ፣
- ባሎች የሚፈልጉትን እጩ ሚስቶቻቸው እንዲመርጡ ማስገደድ፣
- በስልጣን ላይ ያለ ፓርቲ ደጋፊዎች የመንግስት ፕሮግራሞችን/መዋቅሮችን በመጠቀም ማስፈራራት፣
- ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት በሚኖረው ረዥም ሰልፍ ምክንያት መገፋትና መጎተት፣
- እንደ ሰሚ ኮሚቴ አባልነት በሚሰሩበት ወቅት ወደ ቤት ለመመለስ መዘግየት ሲያጋጥም ከቤት መባረር እና

[3] ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው በድጋሚ

[4] ዩኤን ውሜን እና ዩኤንዲፒ እ.ኤ.አ 2018, በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከል የፕሮግራም መመሪያ

[5] የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስእ.ኤ.አ 2023፣ በኢትዮጵያ በአራት ክልሎች ማለትም አዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ የተሰራ ጥናት

♦ ማህበራዊ ሚዲያና ስልክን በመጠቀም ውንጀላ፣ ስድብና ወከባ ማድረስ

ከላይ የተጠቀሱት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ምሳሌዎች ምንም እንኳን የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በበቂ ሁኔታ ባያሳዩም በምርጫ ዑደት ውስጥ የሚፈጸም ፆታዊ ጥቃት ድንበር ተሻጋሪ ኢትዮጵያን ጨምሮ በሁሉም ሀገራት የሚከሰት እንደሆኑ አመላካች ናቸው። የቀረቡት መረጃዎችም በምርጫ ዑደት ውስጥ የሚፈጸም ፆታዊ ጥቃት ሴቶች ከስነልቦናዊ ጉዳት እስከ ሞት ዋጋ የሚያስከፍላቸው ጉዳዩ እንደሆነ ለመረዳት አሳዩ ምሳሌዎች ሲሆኑ ይችላሉ። ሴቶች በምርጫ ጊዜ የፖለቲካ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሚደርስባቸው ስነ-ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ወሲባዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ለጉዳት ብሎም ለሞት ያደርሳቸዋል።

## 4. በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ለምን መስራት ያስፈልጋል?

በተለያዩ ጥናቶች ላይ እንደተገለጸው በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የሴቶችን የፖለቲካና የምርጫ ተሳትፎ ከሚገድቡ ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ። በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የሚያደርሱት የረዥም ጊዜ ተጽእኖ ሴቶች በፖለቲካና በምርጫ እንዳይሳተፉ የሚያደርግ መሆኑም ተለይቷል። በተለይም በእጩዎች ላይ የሚያሳድረው የረዥም ጊዜ ተፅዕኖ ተስፋ መቁረጥና ከፖለቲካ መውጣት ሲሆን መራጮች ደግሞ ለመረጡት ፓርቲ ድምጻቸውን መስጠት አለመቻል ነው። በተጨማሪም የሴቶች ውክልና አለማግኘትና በምርጫ ሂደት ውስጥ አለመሳተፋቸው ሰብዓዊ መብቶችን የመጠበቅ መሰረታዊ መርህን በተለይም የመምረጥ፣ የመመረጥና በመንግስት ውስጥ የፖለቲካ ቦታ የመያዝን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች የሚጥስ ነው።

እነዚህንና መሰል ጉዳዮች ላይ መስራትና በፖለቲካ እንቅስቃሴና ምርጫ ሂደት ውስጥ ሴተቶች ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው። በተጨማሪም የፖለቲካና የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ መድረኮችን ከጥቃት የፀዱ በማድረግ ሴቶችን ወደ ፖለቲካና ዲሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ የሚገቡበትን እድል ማስፋት ብሎም ወደ መሪነት እንዲመጡ ማበረታታት ያስፈልጋል። በምርጫ፣ በፖለቲካና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ የሴቶችን ሚዛናዊ ተሳትፎና ውክልና በማረጋገጥ መንግስታት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊን ጨምሮ በርካታ ጥቅሞችን ሊያገኙ ይችላሉ። ስለሆነም የሴቶችን የፖለቲካና የምርጫ ተሳትፎ ለማሳደግ አግባብነት ያላቸውን መከላከያና ምላሽ መስጫ ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ በፖለቲካ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ መስራት አስፈላጊ ነው።

## 5. መቼ እና እንዴት የሴቶችን ላይ በፖለቲካ/በምርጫ የሚፈጸሙ ጥቃቶች እንከላከል?

በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ጽንሰ-ሀሳብ፣ መንስኤዎቹና የሚያስከትላቸውን ችግሮች ብሎም ችግሩን የመፍታትን አስፈላጊነት ከተረዳን በኋላ የሚቀጥለው እርምጃ መቼ እና እንዴት ጥቃትን መከላከል ወይም ምላሽ መስጠት አለብን የሚለውን ማቀድ ነው። በሌላ አነጋገር በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት ማለት ነው።

## 5.1 በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል መቼ እርምጃ መውሰድ አለብን ?

ሴቶች የፖለቲካና ሴሎችንም ተግባራት ሲያከናውኑ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ያጋጥማቸዋል። አንዳንድ ጊዜ በፖለቲካ ድርጊታቸው ወይም በዝንባሌያቸው ምክንያት ትኩረት ይደረጋሉ እንዲሁም በሌላ ጊዜ ደግሞ በፖለቲካና በምርጫ የሚሳተፉ ሴቶች በመሆናቸው ምክንያት ኢላማ ይደረጋሉ። በሁሉም የምርጫ ዑደቶች ውስጥ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመፍታት የምርጫን ዑደትን ተከትለው የሚከሰቱ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መረዳት፤ መከላከል እንዲሁም ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው፡-

**በቅድመ-ምርጫ ጊዜ፡-**

- የምርጫ ሕጎችን፣ መመሪያዎችን፣ ማኑዋሎችን፣ የሲቪክ ትምህርትን ይዘትና የመራጮች ትምህርት ፕሮግራሞችን (ይዘትና ቋንቋ) በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ ጥቃቶች አንፃር በመቃኘት ማሻሻል/መከለስ፣
- የፓርቲ ውስጣዊ ሰነዶችን መመርመር፣
- በሴቶች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን/ችግሮችን መለየትና ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- የጾታ ውክልናው የተመጣጠነ (ተመጣጣኝ የሆነ የወንድና ሴት ጥምርታ ያለው) የምርጫ አስፈጻሚ ሰራተኞች/የጸጥታ አባላትን ምደባ ማረጋገጥ፣
- በምርጫ ወቅት ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ምላሽ ለሚሰጡ አካላት ጉዳዩን እንዴት በጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸው አስፈላጊውን በስርዓተ-ጾታ እውቀት የተቃኘ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- ከፖለቲካ ተሳትፎ ወይም ከምርጫ ተሳትፎ ጋር በተያያዘ ጥቃት ባጋጠመ ጊዜ ሪፖርት የሚደረግበት የነፃ የስልክ ጥሪ መስመርን በስራ ላይ ማዋል፣
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን አመላካች መለኪያዎች በምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾች ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥና
- ስርዓተ ፆታን ከግምት ውስጥ ያስገባ ለሴት መራጮች አመቺ የሆነ የምርጫ ጣቢያን ማቋቋም።

**ምርጫ በሚካሄድበት ቀን፡-**

- የድምጽ መስጫ ሰልፎች ለሴቶችና ለወንዶች የተለያዩ መሆናቸው አስፈላጊ ከሆነ መለየት፣
- በምርጫ ጣቢያው ዙሪያ በቂ ብርሃን መኖሩን ማረጋገጥ፣
- ለነፍሰ ጡሮች ፣ ለሚያጠቡ እናቶችና የአካል ጉዳት ላለባቸው ቅድሚያ መስጠት ፣
- በሴቶች ላይ ማንን እንደሚመርጡ ምንም ዓይነት ጫና አለመኖሩን ማረጋገጥና፤
- በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ተጎጂዋን ማዕከል ባደረገ ዘዴ ማስተናገድ (ከተከሰተ) ብሎም ክስተቱ በመረጃ ቋት ውስጥ ዩቀመጥ ዘንድ እንዲሁም ክስተቶችን ለመተንተንና ለመከታተል እንዲያመች ለኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ አስፈላጊውን ሂደት ተከትሎ ሪፖርት ማድረግ።

**በድህረ-ምርጫ ጊዜ፡-**

- ለድህረ ምርጫ ግምገማ ማስጥሪዋ በሆነ መልኩ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ

ጥቃቶች ላይ መረጃን መሰብሰብ፣ መተንተንና መጠቀም፣

- ➢ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ሰፊ ጥናቶችን ማካሄድ እና
- ➢ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት ተጨማሪ የመከላከልና ምላሽ መስጫ ዘዴዎች ላይ ስትራቴጂ ማውጣት

ከላይ የተቀመጠው ዝርዝር ሁሉንም አስፈላጊ እርምጃዎች እንደሚካተተ መረዳት ያስፈልጋል:: እንዲሁም አንዳንድ ተግባራት ግልጽ የሆነ ሂደት ላይኖራቸው እንደሚችል ማሰብና በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የምርጫ ሂደቶች ውስጥ መከናወናቸውን ሊቀጥሉ የሚችሉ መሆናቸው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በምርጫ ወቅት በሰሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን በዝርዝር ማጥናት በሁሉም የምርጫ ሂደቶች ውስጥ ሊከናወን የሚችልና የሚገባ ተግባር ነው።

## 5.2 በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል እንዴት መስራት ይቻላል?

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት (VAWiE) በሴቶችም ሆነ በሀገራዊ ልማት ላይ አሉታዊ ተጽእና የሚያሳድር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ችግሩን መፍታት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የሶስት-ደረጃ ስትራቴጂን በመጠቀም በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከልና ምላሽ መስጠት ይቻላል።

ደረጃ 1፡ ክፍተቶቹን/አጋላጭ ነገሮችን መፈተሽ
ደረጃ 2: መከላከልና
ደረጃ 3: ምላሽ መስጠት

በየደረጃው በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚከናወኑ የተለያዩ ተግባራት አሉ።

### ደረጃ 1፡ አጋላጭ ሁኔታዎችንና ሀብትን መለየት

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመመዘን የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎችና ማዕቀፎች በአገልግሎት ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡-

- ♦ ዓለም-አቀፍ የምርጫ ስርዓቶች ፋውንዴሽን (IFES) በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ግምገማ መሳሪያና [ የዓለም-አቀፍ የምርጫ ስርዓቶች ፋውንዴሽን፣ የኤሳኤአይዲ (2016). በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች፤ የግምገማ, ክትትልና ምላሽ መስጫ መሳሪያ ]
- ♦ የተባበሩት መንግስታት የሴቶች ድርጅት (የኤን ውመን) በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከያና ማስወገጃ ማትሪክስ

የዓለም-አቀፍ የምርጫ ስርዓቶች ፋውንዴሽን (IFES) የምዘና መሳሪያ በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን የተባበሩት መንግስታት የሴቶች ድርጅት ማዕቀፍ ግን የድርጊት መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት አገልግሎት ላይ የሚውል መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል። እነዚህን መሳሪያዎች በጥምረት መጠቀም በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶችንና አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ለመለየትና አጠቃላይ ግምገማ ለማድረግ ዕድል ይሰጣል።

---

[6] የዓለም-አቀፍ የምርጫ ስርዓቶች ፋውንዴሽን፣ የኤሳኤአይዲ (2016). በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች፤ የግምገማ, ክትትልና ምላሽ መስጫ መሳሪያ

በተጨማሪም በአገር አቀፍ ደረጃ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ ጥቃቶች አንጻር የሕግ ትንተና ማድረግ አስፈላጊ ነው። በእነዚህ የግምገማ መርሆዎችና መሳሪያዎች ላይ በመመስረት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (2023) አማካኝነት በተካሄደው ሀገር አቀፍ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ጥናትና ምርምር ወቅት አጠቃላይ የሕግ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ውጤቶቹም ከዚህ በታች ቀርበዋል።

ሰንጠረዠ 6. በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ ህጎችና ያሉ ክፍተቶች

| የሕግ ሰነድ | በተግባር ላይ የዋሉ | ያሉ ክፍተቶች | ምክረ-ሀሳብ |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2019 | የሴቶች የፖለቲካ መብቶችን አካቶ ይዟል። | በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን እንደ ተለየ ወንጀል አልተጠቀሰም። | በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ምንነት በግልፅ ለመተርጎምና ወንጀል ለማድረግ ማሻሻል፤ ወይም በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የሚከለክል ወይም ወንጀል የሚያደርግ አዲስና ራሱን የቻለ ህግ ማፅደቅ። |
| የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የጸጥታ ሰራተኞች የስነ-ምግባር ደንብ (2021) | የጸጥታ ሰራተኞች ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል አለባቸው። | ወሲባዊ ጥቃት ብቻ ተካቷል (ሌሎች የጥቃት ዓይነቶች ግን አልተካተቱም)። | እንደ ስነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካላዊ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት አይነቶችን ማካተት። |
| የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ | በአጠቃላይ ጾታ ተኮር ጥቃትን ወንጀል ያደርጋል። | የፖለቲካ ትንኮሳን አያካትትም። | በምርጫ ሂደት ውስጥ የሚደርሱ ጾታ ተኮር ጥቃቶችን ወንጀል ለማድረግ የህግ ማሻሻያ ማድረግ። |

ምንም እንኳን የሴቶችን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች የመሳተፍና ተጠቃሚ የመሆን መብትን ያካተቱ የስርዓተ -ጾታ እኩልነት የህግና የፖሊሲ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የምርጫ አዋጁ ግን በፖለቲካ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጾታ ተኮር ጥቃቶችን ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ግምት ውስጥ ማስገባት አልቻለም። በዚህም ምክንያት በፖለቲካ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት በመቀበል ጉዳዩን በግልፅ ያካተተ ሰነድ  የለም።

### ደረጃ 2 እና 3፡ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከልና ምላሽ መስጠት

በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መስራት ይችላሉ።

- የመከላከልና ምላሽ የሚሰጡ ተግባራትን የሚመራ ጥምረት መመስረት፣
- እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚውል ሀብት መመደብ፣
- በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የተጋላጭነት ሁኔታና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ሀብቶች መለየት፣
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ያለውን አረዳድ ለመጨመር ሰፊውን ማህበረሰብ ዒላማ ያደረገ የግንዛቤ መፍጠሪያ እንዲሁም የንቅናቄ መድረክ ማዘጋጀት፣
- የመንግስት አካላትን ጨምሮ ለቀልፍ ባለጉዳዩ አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
- በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ከመከላከልና ምላሽ ከመስጠት አንፃር የሕግ ኦዲት ማድረግ፤ ክፍተቶችን በህግ ግምገማ መለየትና ክፍተቶቹን የሚሞሉ ህጎችን ማውጣት፤
- ጥቃት ለደረሰባቸውን ሰዎች ግልጽ የሆነ የሪፖርት ማድረጊያ ዘዴን በስራ ላይ ማዋል እንዲሁም የቅብብሎሽ መመሪያ ማዘጋጀት፣
- በፖስታ ፣ በስልክ ፣ በስልክ አጭር የጽሁፍ መልዕክት ፣ በኢሜይል ፣ በበይነ-መረብ ወዘተ. . . መረጃን ለማጋራት የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን ማዘጋጀት፣
- ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች- ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎችን ማዕከል ያደረገ ዘዴን በመጠቀም አገልግሎቶችን ተግባራዊ ማድረግ (የነጻ የስልክ ጥሪ አገልግሎት፣ የቀሬታ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን፣ የአንድ ማዕከላት አገልግሎትንና ሌሎችም ማሰልጠን) ፤2
- ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች የቃለ መጠይቅ አደራረግ ቴክኒኮችን፣ የመረጃ አያያዝና ሌሎችንም የአስፈላጊ ጉዳዮችን አያያዝ የተመለከተ ስልጠና ለአገልግሎት ሰጭዎች መስጠት እና
- በጾታና በስርዓተ-ጾታ የተተነተኑ መረጃዎችን ለመከታተል፣ ለመገምገምና ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ዘዴዎች ማዘጋጀት፤
- በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲሁም የተገኙ ልምዶች በመቀመር ለቀጣይ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ማሻሻያ ግብአት የሚሆኑበትን ስርዓት መፍጠር።
- በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲሁም የተገኙ ልምዶች በመቀመር ለቀጣይ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ማሻሻያ ግብአት የሚሆኑበትን ስርዓት መፍጠር።

እ.ኤ.አ በ2023 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በተመለከተ የሰራው ጥናት እንደሚያሳየው በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት

[7] ተጠቂውን ማዕከል ያደረገ ዘዴ ስርዓተ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት- ጥቃት ከደረሰባቸው አካላት ጋር ለመስራት ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ፣ መብታቸውን ያከበረ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፤ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ማለት የተጠቂዎችን ምርጫና የመረጃ ማካፈል ሁኔታ የዘዴው ዋና አካል ነው

ቅሬታዎች ለመፍታት የሚያስችል ጥቃት የደረሰበትን አካል ማዕከል ያደረገ ዘዴ ውስንነት አለ። በአዎንታዊ መልኩ ደግሞ በምርጫ ደንቡ የቀረበው የቅሬታ ማስተናገጃ ዘዴ ምላሽ ሲሆን የሚችል ነበር። በዚህም መሰረት በአጠቃላይ ምርጫን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በተለያዩ እርከኖች – በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልልና በቦርድ ለማስተናገድ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል። ይህ ዘዴ ወደፊት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ምላሽ ለመስጠት ጥሩ የመግቢያ መንገድ ሲሆን ይችላል።

በምርጫ ቦርድ የተገለፀው የምላሽ መስጫ ዘዴ ይሄ ቢሆንም፣ በአንዳንድ ቦታዎች በምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አልነበረም፣ በዚህም መሰረት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የተመለከቱ ልዩ ቅሬታዎችን ለመቀበል የሚያስችል ዘዴ አልነበረም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባደረገው ጥናት እንዳመለከተው፣ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የተመለከቱ ቅሬታዎችን (በቅድመ ምርጫና የምርጫ ቀን) በስልክና በአካል የጉዳዩ መለያና ምላሽ መስጫ መመሪያ መሰረት በማድረግ ተቀብሏል። እንደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ገለጻ ለምርጫ ቦርድ ቀርቦ በተለያዩ እርከኖች ፍርድ ቤት የቀረቡ ክሶች ከፊሎቹ የተዘጉ ሲሆን ከፊሉ ደግሞ ተቋርጠዋል። እንዳጠቃላይ ከጉዳዩ ጋ በተያያዘ የእርዳታ/መፍትሔ አፈላላጊዎች ቁጥር አነስተኛ ሲሆን መፍትሔ ያፈላለጉ ሴቶችም በአብዛኛው ቅሬታቸውን በተለይ ለፖሊስ ጣቢያዎች አቅርበዋል፡ ፡ ሌሎች መፍትሔ ፈላጊዎች፤ በሁሉም የምርጫ ዑደቶች (ቅድመ ምርጫና ድህረ ምርጫ) ውስጥ ቅሬታቸውን ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት፤ ለምርጫ ጣቢያ አስተዳደር፤ ብሎም ለባህላዊ መሪዎች አቅርበዋ። ይህም የቅሬታ ሪፖርት የተደረገው መደበኛ ባልሆነ (በቃል)ና መደበኛ በሆነ ደግሞ በጽሁፍ ሲሆን አብዛኞቹ አጥጋቢ ምላሽ አግኝተናል ብለዋል። የተወሰዱት እርምጃዎች በአብዛኛው የቃል ማስጠንቀቂያዎች ነበሩ።

## ６. በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ምላሽ መስጠት የሚችሉ አካላት እነማን ናቸው?

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በቤተሰብ፣ በማህበረሰብና በመንግስት ደረጃ የሚፈጸም ሲሆን ድርጊቱን ማንም ይፈጽመው ማን በፖለቲካ ህይወት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ሁሉ መከላከል ብሎም ተገቢና ውጤታማ ምላሽ መስጠት የመንግስት ግዴታ ነው። ስለዚህ መንግስት በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

የመከላከልና ምላሽ የመስጠት ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን በምርጫ ቦርድ የሚመራ ጥምረት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መመስረት ወሳኝ ነው። ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት መካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የፍትህ ዘርፍ፣ የፀጥታና

ደህንነት ዘርፍ፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በሴቶች የሚመሩና የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዩ ጉዳዩ ሚኒስቴር እና ሌሎችም ይገኙበታል።

### ሀ) የዋና ባለድርሻ አካላት ሃላፊነት

### የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና

- የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለዩቶ የሚያስቀምጥ እንዲሁም የሚከለክል መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ለሴቶች እጩዎች ለምርጫ ቅስቀሳ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ በእኩልነት እንደሚደርሳቸው ማረጋገጥ፣
- የፓርቲ መሪዎችንና አባላትን ለስርዓተ-ጾታ ትኩረት የሚሰጥ የቅስቀሳ ስራ ላይ ስልጠና መስጠት፣
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በውስጣዊ አሰራር መከታተልና ሪፓርት ማድረግ እንዲሁም ፈጻሚዎች ተገቢዉን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ።

### የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሚና

- በምርጫ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ውስጥ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከልን ማካተት፣
- በምርጫ ታዛቢነትና በምርጫ ሰራተኛነት የሴቶችን እኩል ውክልና ማረጋገጥ፣
- በምርጫ ጊዜ ለሚገጥሙ ጥቃቶች አስተማማኝ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ።

### የምርጫ ባለስልጣናት

- የምርጫ ጣቢያ ተደራሽ እንዲሁም ለሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከለከል እንዲሁም ምላሽ ላዩ ያተኮረ ስልጠና ለምርጫ ሰራተኞች  መስጠት፣
- ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች ማዕከል ያደረገ ምላሽ መስጫ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ።

### የፖሊስና ደህንነት አካላት ሚና

- ለሴት መራጮችና ተመራጮች አስፈላጊውን ጥበቃ ማድረግ፤
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚደርሱ ጥቃቶችን በፍጥነትና ያለማዳላት መመርመር፤ ወደ ፍትህ አካላት ማቅረብና ምላሽ እንዲሰጣቸው ማድረግ፤
- የፖሊስና ደህንነት አባላት ስለ ስርዓተ ፆታ፤ ስለ ሴቶች መብት እንዲሁም የጥቃት ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ከምርጫ ቦርድ እንዲሁም ከፍትህ አካላት ጋር በመተባበር በምርጫ ወቅት ለሚፈፀም ጥቃት የተቀናጀ ምላሽ መስጠት።

ለ) የሴሎች ባለድርሻ አካላት ሃላፊነት

ሴት እጩዎች

- በቅስቀሳዎች ወቅት ማንኛውንም ማስፈራሪያ ወይም ትንኮሳ ሲደርስ ሪፓርት ማድረግ፣
- ጥቃት በሚደርስ ጊዜ የህግ፣ የማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ መጠየቅ፣
- ከሌሎች ሴት ፖለቲከኞች ጋር መተባበር ፤ ህብረት መፍጠር
- የመገናኛ ብዙሃንንም ሆነ የቅስቀሳ መድረኮች ሲገኑ በምርጫ ወቅት እንዲሁም በፓለቲካ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሴቶች ላዩ የሚደርሱ ጥቃቶችን ማውገዝ፤ ስለ ጉዳዩ ያለውን እውቀትና መረጃ መድኮቹን ተጠቅሞ መጨመር

የሲቪል ማህበረሰብና የመገናኛ ብዙሃን ሚና

- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ የጥቃት ክስተቶችን መከታተል፣ መረጃ መያዝና ሪፓርት ማድረግ፣
- በምርጫ ወቅት የሚከሰቱ ሰርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲሁም አሉታዊ ውጤቶቻቸው ላዩ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣
- ጠንካራ የህግ ጥበቃና ማዕቀፍ እንዲኖር እንዲሁም የተቀናጀ ምላሽ አሰጣጥ እንዲኖር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ላዩ ጫና ማድረግ፣
- ወንድ ልጆችንና ወንዶችን በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል በሚደረገው ትግል ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት።

የትምህርት ተቋማት እንዲሁም ጥናትና ምርምር የሚያካሂዱ አካላት ሚና

- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላዩ የሚደርሱ ጥቃቶችን መነሻ ምክንያት መጠኑንና ተፅእኖውን ለመረዳት ጥናት ማካሄድ፤
- የጥናት ውጤቶች ለፖሊሲ ቀረጻ እንዲሁም ለምላሽ ሰጪ ፕሮግራሞች ግብአት እንዲሆኑ ማድረግ፤
- የሴቶች መብቶችን በተመለከተ በፖለቲካ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ አካላት እና ለማህበረሰብ ክፍሎች ትምህርት እንዲደርስ ማድረግ፡
- ሴቶች በምርጫ ወቅትና በፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች የሚያባብሱ ጎጂ የማህበረሰብ ልምዶች እንዲቀረፉ የሚያስችሉ የውይይት መድረኮችን ማመቻቸት።

Address:
+251952048277
newaethiopia@gmail.com
@newaethiopia
www.newaethiopia.org
Infront of Gibson Academy, Kebele 24,
Addis Ababa, Ethiopia
P.O. Box 19357